**የጨቅላነት ጊዜ ትምህርት ክፍል**
**የዋሽንግተን የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናት የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ**
**(Washington Early Support for Infants and Toddlers (ESIT)) ፕሮግራም**

P. O. Box 40970 | Olympia, WA 98504-0970
ድምጽ (360) 725-3500 | TTY(መስማት ለተሳናቸው) (360) 407-1087 | ፋክስ (360) 725-4925
www.del.wa.gov/esit

# መደበኛ የግጭት አፈታት መጠየቂያ

| **ቅሬታውን ያቀረበው ግለሰብ ወይም ድርጅት ሥም** | | | **ቀን** |
|---|---|---|---|
| **አድራሻ** | | | |
| **ከተማ ግዛት ዚፕ ኮድ** | | | |
| **የልጅ ሥም/የትውልድ ቀን/አድራሻ** | | **የቤተሰብ መረጃ አስተባባሪ** | **የአካባቢ መሪ ኤጀንሲ** |
| **የስልክ ቁጥር(ሮች)** | **የፋክስ ቁጥር(ሮች)** | **የኢሜይል አድራሻ** | |

የዚህ ቅጽ ዓላማ አንድን አለመግባባት ለመፍታት አግባብ የሆኑ ሂደቶችን ለማስጀመር የተመረጡ የግጭት መፍቻ አማራጭ(ጮች)ን (ግልግል፣ የክስ መስማት ሂደት፣ እና/ወይም አስተዳደራዊ የቅሬታ መስማት ሂደት) በሰነድ መዝግቦ መያዝ ነው። እባክዎ በዚህ ቅጽ ላይ የሚጠየቁትን መረጃዎች ይስጡ፣ ይፈርሙ፣ ቀን ይጻፉ እና ከዚህ በላይ በተዘረዘረው አድራሻ ይላኩት። ወላጆች የቤተሰብ መረጃ አስተባባሪን፣ የአካባቢ መሪ ኤጀንሲን፣ ወይም የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናት ድጋፍ ፕሮግራም (ESIT) ሠራተኞችን በማነጋገር ይህንን ቅጽ በመሙላት ሂደት ላይ እገዛ ሊያገኙ ይችላሉ። የግጭት አፈታት አማራጮች መግለጫ በ *IDEA ክፍል ሐ የሥነ-ስርዓት ጥበቃዎች (የወላጅ መብቶች)* ሰነድ ውስጥ ይገኛል።

| **መደበኛ የግጭት መፍቻ አማራጭ(ጮች)** | |
|---|---|
| ☐ | **ግልግል ብቻ**<br>ግልግል ለብቻው ለመደበኛ የክስ መስማት ሂደት ወይም ለአስተዳደራዊ የቅሬታ አቀራረብ ማመልከቻ ከማቅረብ በፊት ሊጠየቅ ይችላል ወይም መደበኛ የክስ መስማት ሂደት ወይም አስተዳደራዊ የቅሬታ አቀራረብ ማመልከቻ ሲቀርብ አብሮ ሊቀርብ ይችላል። ይህን ጉዳይ በግልግል ብቻ ለመፍታት መሞከር ከፈለጉ እባክዎ በዚህ ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ። |
| ☐ | **መደበኛ የክስ መስማት ሂደት**<br>ከመደበኛ የክስ መስማት ሂደቱ በፊት በመጀመሪያ ግጭቱን በግልግል ለመፍታት መሞከር ከፈለጉ በዚህ ሳጥ ላይ ምልክት ያድርጉ። |
| ☐ | **አስተዳደራዊ ቅሬታ**<br>ቅሬታው ከመመርመሩ በፊት በመጀመሪያ ግጭቱን በግልግል ለመፍታት መሞከር ከፈለጉ በዚህ ሳጥ ላይ ምልክት ያድርጉ። |

| ቅሬታው የቀረበበት አገልግሎት ሰጪ/ድርጅት | |
|---|---|
| የEIS አገልግሎት ሰጪ ሥም/ለልጁ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው ድርጅት | |
| አድራሻ | |
| ከተማ ግዛት ዚፕ ኮድ | |
| ስልክ ቁጥር | የኢሜይል አድራሻ |
| ሌሎች በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች (ካሉ) | |

| የአለመስማማት መግለጫ |
|---|
| እባክዎ ከቀረበው ወይም ከተከለከለው የአገልግሎት ጅማሬ ወይም ለውጥ ጋር በተያያዘ ልጁ ያለበትን ችግር በመግለጽ የጽሁፍ ማብራሪያ ያቅርቡ። |

| የአለመስማማት መግለጫውን የሚደግፉ ፍሬ ነገሮች |
|---|
| እባክዎ የእርስዎን የአለመስማማት መግለጫ የሚደግፉ ፍሬ ነገሮችን መግለጫ የጽሁፍ ያቅርቡ እንዲሁም ስጋቶችዎን ለማረጋገጥ የሚረዱ ማናቸውንም ወሳኝ መረጃዎች ይለዩ (ለምሳሌ፣IFSP፣ በጽሁፍ የተደረጉ የመልዕክት ልውውጦች፣ ግምገማዎች/ምዘናዎች) ። በተቻለ መጠን በዋናው ጉዳይ ላይ ያተኩሩ። |

| ለስጋት(ቶች) የቀረበ(ቡ) መፍትሄ(ዎች) |
|---|
| ቅሬታውን ያቀረበው ሰው በወቅቱ ሊያውቃቸው ወይም ሊያገኛቸው በቻለ መጠን የቀረበውን መፍትሄ በጽሁፍ ገልጸው ያቅርቡ። |
| ግልግልን እና/ወይም መደበኛ የክስ መስማት ሂደትን ከመረጡ እባክዎ በቀጣዮቹ ሁለት ሳምንታት ውስጥ እርስዎ ሊገኙ የሚችሉባቸውን ቀናት እና ጊዜያት ይምረጡ። |

| **ፊርማ** | **ቀን** |
|---|---|
| | |

ቅሬታውን ያቀረበው ወገን ከመሪ ኤጀንሲው ዘንድ ቅሬታውን ባቀረበበት በተመሳሳይ ጊዜ የቅሬታው ኮፒ የEIS አገልግሎትን ለሚሰጠው ኤጀንሲ ወይም አገልግሎት ሰጪ መስጠት አለበት።

ፌብሩዋሪ 2012